የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 19
ADDIS ABABA, 21st March, 2024

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፵፪/፪ሺ፲፮

ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ …………………………………...ገጽ ፲፭ሺ፫፻፳፰

## ደንብ ቁጥር ፭፻፵፪/፪ሺ፲፮

## ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ለማቋቋም የወጣውን ደንብ ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፳፩ እና አንቀጽ ፵፯(፬) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፵፪/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ማሻሻያ

ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ደንብ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፺፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

## Content

Regulation No. 542/2024

The National Veterinary Institute Establishment Amendment Council of Ministers Regulation ……......................................................Page 15328

## REGULATION NO. 542/2024

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE NATIONAL VETERINATY INSTITUTE AS PUBLIC ENTERPRIZE ESTABLISHMENT REGULATION

The Council of Ministers has issued this Regulation pursuant to Article 21 and Article 47(4) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "The National Veterinary Institute Establishment Amendment Council of Ministers Regulation No. 542/2024”.

### 2. Amendment

The National Veterinary Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 52/1999 is hereby amended as follows:

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፡፡

፮/ <u>ካፒታል</u>

"ለብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት የተፈቀደው ካፒታል ብር ፪ ቢሊዮን ፭፻፷ ሚሊዮን ፲፮ ሺ ፪፻፴፪ (ሁለት ቢሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ሚሊዮን አሥራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፮፻፵ ሚሊዮን ፬ሺ ፶፰ (ስድስት መቶ አርባ ሚሊዮን አራት ሺህ ሃምሳ ስምንት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡"

፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

1/ Article 6 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 6.

**"6/** **<u>Capital</u>**

The authorized capital of the National Veterinary Institute shall be Birr 2,560,016,232 (Two Billion Five Hundred Sixty Million Sixteen Thousand Two Hundred Thirty Two Birr) of which 640,004,058 (Six Hundred Forty Million Four Thousand Fifty Eight Birr) is paid in cash and in kind."

**3. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 21st Day of March, 2024.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**